የሰ.መ.ቁ 232953

ቀን ጥቅምት 6 2016ዓ.ም

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

አመልካቾች፡ 1ኛ. ወ/ሮ ሀልችቱ ዳላቻ

2ኛ. ወ/ሮ ደራርቱ ቦቶንካ | አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡ 1ኛ. አቶ ጋልፋቶ ጊዶሳ

2ኛ. አቶ አበራ አርስቻ / አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ የቀረበው አመልካቾች የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሀዋሳ ዙሪያ ወረዳ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 14066 በ23/11/11ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ፤ የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሀዋሳ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድቤት በመ.ቁ 49773 በ20/5/13ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ፤ የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 00835 በ4/10/13ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ

ማ ሰታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ አንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 01671 በ16/9/14ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት በ10/12/14ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አመልካቾች በስር የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሀዋሳ ዙሪያ ወረዳ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት ክስ አመልካቾች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ለረጅም ግዜ ጋብቻ መስርተን ይዞታና ንብረት አፍርተን አልምተን ስንጠቀም ቆይተናል፡፡ ካለን ይዞታ ውስጥ አንዱ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር የጋራ ሀብታችን የሆነውን አዋሳኞቹ በክሱ የተጠቀሱትን ይዞታ በቆሎ ዘርተን በየአመቱ የምንጠቀመው አለን፡፡ ይህን ይዞታችንን ባለቤታችን የሆነው 1ኛ ተጠሪ በምን ሁኔታ እንዳሳለፈ አናውቅም፡፡ 2ኛ ተጠሪ አመልካቾች ሳናውቅ ከ1ኛ ተጠሪ አግኝቻለሁ ብሎ የአመልካቾች ፈቃድ ሳይኖር ገብቶ ሲሰራ እንዳይሰራ እና የሚሰራውንም ለምን ትሰራለህ ስንል 1ኛ ተጠሪ እንደሰጠው በመግለጽ ይህን ይዞታችንን ከ2010ዓ.ም ጀምሮ እንዳንጠቀም ከልክሎናል፡፡ ስለሆነም 2ኛ ተጠሪ ይህን ይዞታችንን ለቆ እንዲወጣ፤ 2ኛ ተጠሪ ይዞታውን ከ1ኛ ተጠሪ በውል ያገኘሁት ነው የሚል ከሆነ በእጃቸው ያለው ውል በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 145 መሰረት ቀርቦ እንዲፈርስ እንዲወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

1ኛ ተጠሪ ባቀረቡት መልስ አመልካቾች ሚስቶቼ ናቸው፡፡ ለረጅም ግዜ ለክሱ መነሻ የሆነውን የጋራ ሀብታችን የሆነውን ይዞታ ይዘን መኖራችን ትክክል ነው፡፡ ይህን የጋራ ይዞታችንን ለእህቱ ልጅ አቶ ጢሞቲዎስ ባራሳ ለሚባለው በቆሎ ዘርቼ እጠቀማለሁ ብሎ ጠይቆኝ በቆሎ ዘርቶ ይጠቀም ብዬ ከሰጠሁት ውጪ ይህን ይዞታ 1ኛ ተጠሪ ለ2ኛ ተጠሪ በቃልም ሆነ በጽሁፍ ውል አልሰጠሁትም፡፡ 2ኛ ተጠሪ ለክሱ መነሻ በሆነው ይዞታ ውስጥ በምን ሁኔታ እንደገባ አላውቅም፡፡ ለ2ኛ ተጠሪ ስለመስጠቱ የሚገልጽ የቃልም ሆነ የጽኁፍ ውል ስምምነት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ 2ኛ ተጠሪ ባቀረቡት መልስ ለክሱ መነሻ የሆነውን መሬት አመልካቾችም ሆነ 1ኛ ተጠሪ ተጠቅመውበት አያውቁም፡፡ ይህ ይዞታ 2ኛ ተጠሪ እስካሁን እየተጠቀምኩበት ያለሁት እና በ2005ዓ.ም የባለቤትነት ማረጋገጫ አውጥቼበት ስጠቀምበት የቆየሁት የግሌ ይዞታ ነው፡፡ በአመልካቾች በሰነድ ማስረጃነት የቀረበው የመሬት ባለቤትነት ማረጋገጫ ትክክል ስለመሆኑ አጠራጣሪ ነው፡፡ ሰነዱ የተሰጠው ለየትኛው ይዞታ እንደሆነ በሜክታርም ተገልጾ የተቀመጠ ነገር የለም፡፡ እንዲሁም በአመልካቾች በሰነድ ማስረጃነት የቀረበው የግብር ካርኒ ክስ ለቀረበበት ይዞታ ሳይሆን በሀዋሳ ዙሪያ ወረዳ ውስጥ በሌላ አካባቢ ላለ ይዞታ የተገበረ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡ ስለሆነም ክሱ ውድቅ እንዲደረግ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድቤቱም ክሱን ሰምቶ ጭብጦችን በመያዝ የአመልካቾችን እና ተጠሪዎች በየራሳቸው ያቀረቧቸውን ምስክሮች ከሰማ በኋላ በግራቀኙ የቀረቡትን የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎች መርምሮ ክርክር የተነሳበት ይዞታ የ2ኛ ተጠሪ መሆኑ በሰው እና በሰነድ ማስረጃ የተጣራ በመሆኑ 2ኛ ተጠሪ ለክሱ መነሻ የሆነውን ይዞታ ለቆ የሚወጣበት ምክንያት የለም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካቾች ከላይ በተገለጸው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሀዋሳ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም የተጠሪዎችን መልስ በመቀበል እንዲሁም ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ይዞታ በተመለከተ ለሀዋሳ ዙሪያ ወረዳ ልማትና የተፈጥሮ ሀብት ጽ/ቤት ትእዛዝ በመስጠት ከጽ/ቤቱ ምላሽ ከቀረበለት በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የስር የወረዳውን ፍ/ቤት ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ በዚሁ ላይ አመልካቾች ይግባኝ ለሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ

ማ ሰታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ፍርድቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍ/ቤቱም የተጠሪዎችን መልስ ተቀብሎ ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍ/ቤቱን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ በአመልካቾች የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተጠሪዎችን መልስ ተቀብሎ የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ከላይ የተገለጹትን ውሳኔዎች በመቃወም ሲሆን ይዘቱም አመልካቾች በስር ፍ/ቤት ባቀረብነው ክስ ተጠሪዎች እርስበራሳቸው የገቡት የትኛውም አይነት የውል ስምምነት በፍ/ቤት ትእዛዝ ቀርቦ እንዲፈርስ የጠየቅን በመሆኑ የስር ፍ/ቤቱ ውል አለ ወይስ የለም? ውል ካለ ይፈርሳል ወይስ አይፈርስም? የሚሉትን ነጥቦች ሊያጣራ ሲገባው ከተጠየቀው ዳኝነት ጋር ግንኙነት የሌለውን የይዞታው ባለቤት ማን ነው? ከየት ነው ያገኘው? የሚሉትን ነጥቦች በመያዝ ጉዳዩን መርቶ ይዞታው የ2ኛ ተጠሪ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 182(2) ድንጋጌን የሚቃረን መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ የስር ፍ/ቤት ለክርክሩ መነሻ የሆነው የገጠር ይዞታ የ2ኛ ተጠሪ ነው በማለት ድምዳሜ ላይ ከመድረሱ በፊት በአንድ ይዞታ ላይ ከሁለቱም ተከራካሪ ወገን የቀረበውን የገጠር ይዞታ ባለቤትነት ማረጋገጫ ከሰጪው መንግስታዊ አካል ትክክለኛው የትኛው ነው የሚለውን ሳያጣራ እና ሳይመረምር በማለፍ የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም አመልካቾች እና 2ኛ ተጠሪ ካቀረብነው ክርክር አንጻር ፍ/ቤቱ እስከ ስፍራው ድረስ ሄዶ የአካባቢውን ሽማግሌዎች አስቀርቦ ማጣራት ሲገባው ይህን ሳያደርግ የሰጠው ውሳኔ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 255፤ 257 እና 272 ከደነገጉት አንጻር መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ ለክርክሩ መነሻ በሆነው ይዞታ ላይ ተጠሪዎች ያደረጉት የቃልም ሆነ የጽሁፍ ውል ስምምነት ካለ ይፈርሳል ወይንስ አይፈርስም? በመካከላቸው ውል ከሌለ 2ኛ ተጠሪ ወደ አመልካቾች ይዞታ የገባበት መንገድ ህጋዊ ነው ወይንስ ህገወጥ ነው፤ 2ኛ ተጠሪ ይዞታውን ከ2010ዓ.ም ጀምሮ የያዘውን ለቆ ይወጣል ወይስ አይወጣም? የሚሉት ጭብጦች ላይ ተገቢውን ማስረጃ በመስማት እና የሀዋሳ ዙሪያ ወረዳ ልማትና የተፈጥሮ ሀብት ጽ/ቤት ትክክለኛው የይዞታ ማረጋገጫ የማነው የሚለውን መግለጫ ቀርቦ እና ፍ/ቤቱ እስከ ስፍራው ሄዶ አጣርቶ እንዲወስን ውሳኔ እንዲሰጥልን፤ ወጪና ኪሳራም እንዲከፈለን እንዲወሰንልን የሚል ነው፡፡

ይህ አቤቱታቸው በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ በስር ፍ/ቤት ግራቀኙ በሚከራከሩበት ይዞታ ላይ ሁለት የባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የቀረበና ከሁለቱ የይዞታ የባለቤትነት ምስክር ወረቀት የክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ የሚያሳየው የትኛው ነው የሚለው ከሚመለከተው አካል ሳይጣራ የስር ፍ/ቤት የምስክር ወረቀቶችን ራሱ አይቶ አንዱ አቅጣጫ ተጠቅሷል አንዱ 4 አቅጣጫ አልተጠቀሰም በማለት ይዞታው የ2ኛ ተጠሪ ነው የመባሉን ተገቢነት ለማጣራት ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ይቅረብ ተብሎ በ22/3/15ዓ.ም በመታዘዙ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎ 1ኛ ተጠሪ በ16/5/15ዓ.ም በተጻፈ ባቀረቡት መልስ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል የሚሉበትን ምክንያት በመዘርዘር በአመልካቾች አቤቱታ መሰረት ውሳኔ ቢሰጥ የማይቃወሙ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ 2ኛ ተጠሪ በ16/5/15ዓ.ም በተጻፈ ባቀረቡት መልስ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አልተፈጸመበትም የሚሉበትን ምክንያት በመዘርዘር እንዲጸና ጠይቀዋል፡፡ አመልካቾች በ7/6/15ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ማ ሰታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ይህ የሰበር ሰሚ ችሎትም የአመልካቾችን የሰበር አቤቱታ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢዎቹ የህግ ድጋጌዎች አንጻር የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) ስር እንደተመለከተዉ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠዉ ሥልጣን ማናቸዉንም መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበትን የመጨረሻ ዉሳኔ በሕግ በዝርዝር በሚወሰነዉ አግባብ መርምሮ እንዲያርም ነዉ፡፡በዚህ የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ ላይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ምንነት በግልጽ አልተደነገገም፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በተለያዩ መዛግብት ላይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሚያሰኙ ምክንያቶችን የሚያመላክቱ የሕግ ትርጉሞች ሲሰጥ ቆይቷል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80(3/ሀ) ስር በሰበር ችሎት የሚታይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ምንነት በተመለከተ ጭምር ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል ተብሎ በተደነገገዉ አግባብ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ላይ “መሠረታዊ የሕግ ስህተት” ለሚለዉ ሐረግ ትርጉም እስከተሰጠበት ጊዜ ድረስ ለሐረጉ በሕግ ትርጓሜ አልተሰጠም ነበር፡፡ ስለሆነም አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ከፀና በኋላ በዚህ ችሎት ዉሳኔ ለሚሠጥባቸዉ ጉዳዮች በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 “ለመሰረታዊ የሕግ ስህተት” የተሰጠዉን ትርጓሜ መመልከት የግድ ይላል፡፡ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2/4 ስር “መሠረታዊ የሕግ ስህተት” የሚያሰኙ ምክንያቶች በዝርዝር እና በጥቅል አገላለጽ ተተርጉሟል፡፡ በዚህ ትርጓሜ ላይ በመንተራስ ከክልል ፍርድ ቤቶች ተጀምረዉ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ሰበር ሰሚ ችሎቶች ታይተዉ በተሰጡ የመጨረሻ ዉሳኔዎች ላይ ተፈጽመዋል ሊባሉ የሚችሉ እና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ታይተዉ ሊታረሙ የሚችሉ መሰረታዊ የሕግ ስህተቶች በአዋጁ አንቀጽ 10(1/ሐ እና መ) ስር ተደንግጓል፡፡

እነዚህም ምክንያቶች *(1)* በአዋጁ አንቀጽ 2(4/ሀ) ስር በተመለከተዉ መሰረት ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌዎችን በሚቃረን አኳኋን በክልል ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ የመጨረሻ ዉሳኔ፤ *(2)* በአዋጁ አንቀጽ 2(4/ሸ) ስር እንደተመለከተዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ በሚቃረን አኳኋን በክልል ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ የመጨረሻ ዉሳኔ፤ *(3)* በአንቀጽ 2(4/ለ) ላይ እንደተመለከተዉ ሕግን አላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉ ድንጋጌ ተጠቅሶ የተሰጠ የመጨረሻ ዉሳኔ ሆኖ ይህ ዉሳኔ የተሰጠበት ጉዳይ ለሕዝብ ጥቅም ሀገራዊ ፋይዳ ያለዉ ጉዳይ በሚል በሕጉ ከተጠቀሱት ሦስቱ ምክንያቶች መካከል ቢያንስ አንዱን የሚያሟላ እና ፍትህን የሚያዛባ ጉልህ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት የመጨረሻ ዉሳኔ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነዉ፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካቾች ባቀረቡት ክስ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር የጋራ ሀብታችን የሆነውን በክሱ የተጠቀሰውን ይዞታ 2ኛ ተጠሪ አለአግባብ ስለያዘ ይዞታችንን ለቆ እንዲወጣ፤ 2ኛ ተጠሪ ይዞታውን ከ1ኛ ተጠሪ በውል ነው ያገኘሁት የሚል ከሆነ ውሉ ቀርቦ እንዲፈርስ እንዲወሰንልን ሲሉ ዳኝነት የጠየቁበት ነው፡፡ ጉዳዩ የተጀመረውም በክልል ወረዳ ፍ/ቤት ሆኖ በክልል ሰበር ሰሚ ችሎት የመጨረሻ ውሳኔ ተሰጥቶበት የቀረበ ነው፡፡ የመጨረሻውን ውሳኔ የሰጠው የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የስር የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሀዋሳ ዙሪያ ወረዳ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በግራቀኙ የቀረቡትን የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎች መርምሮ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ የ2ኛ ተጠሪ መሆኑን በፍሬነገር ደረጃ

በማረጋገጥ 2ኛ ተጠሪ ይህን ለክሱ መነሻ የሆነውን ይዞታ ለቆ የሚወጣበት ምክንያት የለም በማለት የሰጠውን ውሳኔ እና በየደረጃው ባሉት የክልሉ የበላይ ፍ/ቤቶች የጸናውን ውሳኔ በማጽናት ውሳኔ የሰጠበት ነው።

በመሆኑም አመልካች ለዚህ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርበው መዝገቡ የተከፈተው በ12/12/14ዓ.ም በመሆኑ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት የቀረበው የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ከጸና በኋላ ስለሆነ ከላይ በተጠቀሱት የአዋጁ መስፈርቶች አንጻር ሊመረመር የሚገባ ነው። በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ከላይ በተመለከተዉ መሰረት የተሰጠዉ ዉሳኔ ሕገ መንግስቱን የማይቃረን፣አስቀድሞ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሠጠዉን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የማይቃረን፣ ጉዳዩ አገራዊ ፋይዳ አለዉ ሊባል በሚችል የሕዝብን ጥቅም በሚመለከት ጉዳይ ላይ በግልጽ ሕግን አለአግባብ በመተርጎም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉ ድንጋጌ ተጠቅሶ የተወሰነ ነዉ ሊባል የማይችል ጉዳይ ከመሆኑም በተጨማሪ ፍትሕን የሚያዛባ ጉልህ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል የሚያስብል ባለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10(1/ሐ እና መ) ስር የተደነገጉ መስፈርቶችን የሚያሟላ ባለመሆኑ በዚህ ችሎት ደረጃ ተመርምሮ ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም። በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል።

ውሳኔ

1. የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሀዋሳ ዙሪያ ወረዳ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 14066 በ23/11/11ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሀዋሳ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድቤት በመ.ቁ 49773 በ20/5/13ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 00835 በ4/10/13ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 01671 በ16/9/14ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ጸንተዋል።
2. በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ አመልካች እና ተጠሪ የየራሳቸውን ይቻሉ።
3. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ።
4. መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል። ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማ ሰታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም